# የቃሊቲ ትሩፋን

ያገራችን ምሁራን ዘንድሮስ ቦዘኑ
መሆን አቅቶዋቸው ልክ እንደዘመኑ
መሳስሎ ማደሩ መሸም መጀነኑ
በላያቸው ላለው እድሜ እየለመኑ።

እኛ እማናውቀውን መብት የሚባል ነገር
ያልሞካከርነውን መርጦ መተዳደር
እናመጣ ብለው ገብተው ለፉክክር
ታጉረው አረፉት ከወንጀለኛ ጋር።

የኛዋ አቢሲኒያ ጥንታዊቷ አገር
እደርሳልሁ ብላ ከስልጣኔ ድንበር
ሰንቃ ነበረ የቀለም ቅንብር
በውድ ልጆችዋ የጥበብ ማህደር።

ዘመን ያፈራቸው ካድሬና ዳኛዎች
ነጭ ለባሽ ጭቃ ሹም ያገር ዘመናዮች
ዛሬ እሚበጀውን እናውቃለን ብለው
መለከት እምቢልታ ጥሩምባ አስነፍተው
በዩንቨርሲቲ በር ታጣቂ አሰልፈው
ለኮሌጅ ላኪምቤት እንዲሁም ላስኳላው
ቀለም አልፎበታል አቅላሚም አያሻው
ምሁር ምን ያደርጋል ጥያቄው ብዙ ነው
ሲሉ መርዶ አረዱን ልባቸውን ሞልተው።

እኛ ማን አለብን ጠያቂውስ ማን ነው
ጠበንጃ ሽጉጡን በእጃችን ካረግነው
ብለው ተመክተው በያዙት ተኩራርተው
ላኩት አሉ ምሁሩን ቀለም አሸክመው
እልማቱ መንደር ቃሊቲ እሚባለው።

ዩህንን ሲሰሙ ጮቤ ረገጡ አሉ
ቁንጫና ሌሎች ተባዮች በሙሉ
በተለዩም ትሩፋን ከነባለሚሉ።
ከትልቅ ከትንሽ ከሃብታም ከድሃው፡
ከወንጀል ታራሚ ከህሊና እስረኛው
ፍርድ ተጣሞበት በግፍ ከታሰረው
ሁሉን በያዩነቱ ቀምሶ ያጣጣመው

ሌሊትና ቀኑን እረፍት የማያውቀው
የትኳን ዘመናይ ቃሊቲ ያፈራው።
ቀልብ ገዝቷል ዛሬስ እንደምን አደበ
አይነካም አሉ ደም ቀለም ካልጠገበ።

አገር ያፈራችው በወረት በጥሪት
እጅግ የከበረው አንጡራው ያገር ሃብት
ላንተው ቀርቦልሃል ቁርስ ምሳና ራት።
እንግዲህ እፈስው አርገው በጎተራ
ዱመጣል ይዞልህ ሁሉም በየተራ።
አርገው ጎረድ ጎረድ ሲያሻህ በያዱነቱ
በውል አወራርደው እንደየግብአቱ።
ብትፈልግ መሃንዲስ ቢያሻህ ጋዜጠኛ
ቢያምርህ ከአርቲስቱ ከጠበቃ ዳኛ።
ካኪም ከዶክተሩ ከብርቅ አስተማሪው
እድሜልኩን ጥበብ ሲያቀልም ከኖረው
ሁሉም ቀርቦልሃል በደንብ አጣጥመው።
ለኮሌጅ ላኪምቤት አልታደልክም ካለው
ጊዜው ፈቅዶልሃል አንተው ተመገበው
ሃይ ባይ እስኪመጣ ወቅትም እስኪሸረው።

ወገን ግን ተነሳ ዱህን ታገል ከምር
ደግ አሳቢው ነቢይ እንዲከበር ባገር።

*በብርሃኔ ገብረህይወት*